# አጣዳፊ ፀረ-ወያኔ ትግልና
# አገርን ለነፃነት፣ ለመንግሥትና ለሥርዓት ለውጥ በአስተማማኝ የሚያበቃ ሐቀኛና ጠንካራ በብሔራዊ አጀንዳ የትግል መስመር እናድርግ

ከበላይ መታፈሪያ ዶ/ር

ወያኔን ከፀረ-ኢትዮጵያ ድርጊቱ ለማስወጣትና ኢትዮጵያና ሕዝቧ የተነጠቀውን የአገር ባለቤትነትና ነፃነት ለማስመለስና ለማግኘት፤ ሁሉን ባቀፈ ትብብር ኢትዮጵያዊነታችንን፣ ኃላፊነታችንን፣ የታሪክ ተጠያቂ፣ የጎሊና ወቀሳውን እውን አድርገን ከዛሬ የላቀ፣ የደረጀና ግብ የሚያረጋግጥ ጥንካሬና ፅናት፣ ቁርጠኝነትና የፖለቲካ ክላውት ሲኖረንና በአገራዊ ኅብረት ስንሰራ ነው።

ወደ ተግባር እንግባ !

የፀረ-ወያኔ የፖለቲካ ተቃውሞ ችግሩና ዓይነቱ ጥሩ ኢትዮጵያዊ፤ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ጥቅሞች በአሀዳዊ ኢትዮጵያ በአንድ ብሔራዊ ህዝብ በመራራና በቆራጥ ትግል ነጥሮና ጠሎ የትግልና የድርጅት ተመክሮ ባህሪ፣ ያስተዋይነትና ጥበብን የተካነ ዛሬም እንደ ትናንቱ ለኢትዮጵያ የቆሙ፣ የሚያቀርቡት የነጠረ ሀሳብና የሚያመጡት ፍቱን መፍትሔ የትግሉና የድል መመሪያ ሁሉ በወያኔ ላይ አተማማኝ ድልን ያሚያቀዳጅና ሀገርን የሚያድን ህዝቡን ነፃ የሚያወጣ መሆን አለበት። ታጋይና ፖለቲከኛ በዚህ ቀውጢ ሰዓት በዋነኛነት የሚጠቅም ታግሎ የሚያታግል፣ ለተግባራዊነቱ ኃላፊነትና ግዴታን የሚቀበልና ተፍጻሚነቱን በፅናት ለግብ የሚያበቃ ሲሆን ነው። ኢትዮጵያን ከወያኔ እናድን ካልን፤ አርቀን ልናይና የግድ ልንቀበቸው የሚገቡ ሀቆች መሆናቸውን መረዳትና ለተግባራዊነታቸውም በኅብረት መሰለፍ እንዳለብን መገንዘብ ያስፈጋል። ዝም ብሎ ማቀንቀን በየፊናው የፖለቲካ ሽውሽው የትም ስለማያድርሰን፤ ኅብረት ፈጥረን ታግሎ በማታገል ኢትዮጵያን እናድን።

- ኢትዮጵያ እጅግ በአስከፊ የጭቆና ሥርዓት ከወደቀች ይኼው ዛሬ ፳፫ ዓመት ሆናት።
- ኢትዮጵያ ከፋሽስት ጣሊያን ወረራ ወዲህ፤ ሕልውናዋ የሕዝቧ የወደፊት ዕድል ትልቅ አደጋ ላይ የወደቀበት ጊዜ ቢኖር ዛሬ በወያኔ/ኢሕአዴግ ፋሽስታዊ አምባገነን አስተዳደር ነው።
- ዛሬ ኢትዮጵያ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ እጅግ ተዋርዳ፣ ተራቁታና ተጎሳቁላ ትገኛለች። በዚህ ምክንያት ተቆርቋሪ ልጆቿ ጥበብን በመመርኮዝና ፈጣሪ አምላካችንን በመተማመን፤ የሕዝቧን ጭቆናና ስቃይ በማስወገድና ዘለቄታዊ መፍትሔና ብልጽግና ለማስፈን ታጥቀን መነሳት የግድ የሚለን ወቅት ነው።

የሕወሀት/ኢሕአዴግ ጎጠኛና ዘራፊ መንግሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚበጅህን እናውቅልሀለን በማለት በቋንቋ ልዩነት በመሸንሸንና በመለየት፤ የሀገሪቱን ሀብትና ንብረት በመበዝበዝ፤ በሀቅ የቆሙ ልጆቿን በማደን፣ በማሰርና በመግደል፤ የሀገሪቱን ድንበር አሳልፎ በመሥጠት ( በመሸጥ ) ለም መሬቷን በመቸርቸር በጠቅላላው በሕገ_ወጥ አገዛዝ፤ ከባድ የዘረፋና ጭቆና በሀገሪቱ ላይ እየተፈጸመባት ይገኛል። ሕወሀት ወያኔ ህዝቡን በገዛ ሀገሩ ከሥራውና ከመኖሪያ ሥፍራው እያፈናቀለ፤ የሚናገርበትን ቋንቋን የሚኖርበትን ክልል ወስኖለት በሀገርና በሕዝብ ላይ የጥላቻና የልዩነት መንፈስ መርዝ እየረጨና እየበከለ ነው። ወያኔ የሀገሪቱን ህልውና፤ የሕዝቡን አንድነትና ታሪክ ክዶ፤ የነፃነትና የኢትዮጵያ የሕልውና ምልክት የሆነውን ሰንደቅ ዓላማችንን አረንጓዴ ብጫ ቀዩን አዋርዷል፣ ቀዷል፣ አራክሷል።
ወያኔ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ በወራሪነት የመጣ ጠላትና ዘራፊ አጋሚዶ ኃይል ነው። ለአንድነት ሳይሆን ለመበታተን፣ ለመገንባት ሳይሆን ለማፍረስ፣ ለልማት ሳይሆን ለመዝረፍ፣ ለማፋቀር ሳይሆን ለማለያየት የመጣ፤ ፋሽስታዊ ወያኔ ርዕዩተ ሥርዓት፤ በፀረ-ኅብረተሰብ ባህሪ የተመረዘ ጎጠኛ አጥፊና ተንኮልን መመሪያ ያደረገ፤ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊነትን፣ ሰንደቅ ዓላማን፣ በተለይም አማራንና ክርስትና ሃይማኖት ተቀዳሚ ጠላት አድርጎ ለማጥፋትና ሀገሪቱን ወደኋላ ለማስኬድ፤ ሀብቷን እየዘረፈ የሚወስድ የጥቅም ቡድን ኃይል ነው።

ወያኔ በጥላቻ ላይ የተመሠረተ ፀረ-አንድነት ሥርዓት በመሆኑ፤ የእያንዳንዱ በቋንቋ ልዩነት የፈጠረው የጎሳ ፍላጎት፤ በጥቅም ላይ የተመሠረተ ሆኖ፤ የቋንቋ ጎጥ ክልሎች ጥቅማቸውን ለማግኘትና ለማስጠበቅ፤ ከፖለቲካ ኃይሉ ከወያኔ ርዳታ በመሻት፤ ፍራታቸውንና ደህንነታቸውን ይፈልጋሉ፤ ከሚል ያተኮረና መለያየቱን እየተጠቀመበት ያለ የማፊያ ቡድን ሥርዓት ነው። ወያኔ ሕወሀት የተጠነሰሰውና የተጠቀመበት መርዝ፤ የተማረውን፣ አማራውን ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነትን ማጥፋት ነው።

ስለዚህ የዚህ ዓይነት የፖለቲካ አመለካከትና ሥርዓት ተወግዶ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክና ወግ የብሔራዊ የረጅም ሺህ ዘመናት በአንድ አሀዳዊት ኢትዮጵያ፤ አንድ ሀገር ዜጋ ሕዝብ አብሮ የመኖር ባህሉና ፍላጎቱን መሠረት ያደረገ ህግራዊ ማኅበራዊ መዋቅሮችን ከታሪክና ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አንድ አድርጎ ያዛመደ ሕዝብ፤ ኢትዮጵያዊነት ኑሮና

ሕይወትን የሚነካ እምነት፤ ፍላጎትና ተስፋ፤ የኅብረተሰቡ ቅርስ በመሆኑ፤ ኢትዮጵያዊነት በኢትዮጵያ ሀገራዊ እምነት ላይ የተመሠረተ ጽኑ የመብት፣ ነፃነታዊ ፍቅር ነው። ይህን ከባዕዳን ተፅዕኖና ከፋሽስታዊ ወያኔ ጣልቃ ገብነት፣ ዘረፋና ተንኮል ነፃ የሆነ የሀገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስከብር ማኅበራዊ ሥርዓት መመሥረትና መጠበቅ ያስፈልጋል።

እምነትን፣ ትዕግሥትና ፅናትን ፈታኝ በሆነ ዘመን ላይ ነው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የሚገኙት። ይህን በድል አድራጊነት ለመወጣትና አልፈን ለመጪው ትውልድ የተሻለ ዘመን በኢትዮጵያዊነት ለማውረስ ራዕይ ካለን፤ ማድረግ ያለብን ኢትዮጵያዊ ቃል ኪዳን እንደ ቀደምት ትውልዳችን ኃላፊነትና ግዴታን ማጎልበትና ኢትዮጵያዊ ማንነትን በማደስ የዚህ ትውልድ ግዴታችንን ለአንድ ሰኮንድ እንኳን ያለመዘንጋት ለተግባር ዝግጁ መሆን ነው።የኢትዮጵያን አንድነት አጠንክሮ ሕልውናዋን ለመጠበቅ፤ ሞራል፣ ክብርና ኩራቷን ለመመለስ ዛሬም እንደ ትናንቱ አንድነታችን ወሳኝ ኃይላችን ነው።

ኢትዮጵያዊያን ትውልድን በኢትዮጵያ ማንነቱና ሥነ ምግባር ኢትዮጵያዊ ወግና ባህል ለመቅረፅና ለማነጽ ዝግጁዎች በመሆን ሥርተን የምናሳየው፣ የምናስተምረው የራሳችን አኩሪ ሥራ ሲኖረን እንጂ፤ ሌላው የሠራውን ታላቅና መልካም ምግባር በማወደስ ወይንም በመኮነን፤ የራሳችንን ባዶ አድርገን፤ ባዶነትን ለመጪው ትውልድ እንዳናወርስ ልንሰጋና ልንጨነቅ፣ ልናደርገውም ወቅቱ አሁን እንደሆነ ይገባን።

በሀሰት የአንድነት ታሪክን ከመናድ፣ በውሸትና በተንኮል የአዘቅት ቁልቁለትን ከመንደርደር፣ጠላት ያጨቀየውን መንገድ ትተን ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማንነቱን፣ ምንነቱንና ምን እንደሚፈልግና ምን ማድረግ እንደሚሻ ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል። ምንጊዜም ሀገሩን ኢትዮጵያን፣ አንድነቱን ኢትዮጵያዊነቱን፣ ሰንደቅ ዓላማውን፣ ክብሩንና አሀዳዊ ኅብረተሰብዊ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን ነው።

በባዕድ ቴዎሪና ፍልስፍና ማጥ ውስጥ የዘቀጠ የአፍራሽ ኃይሎች ቅጥረኛ የሆኑ ግለሰቦችና ደርጅቶች ይህንን የስታሊኒስት ቋንቋ እየተናገሩና መመሪያ እያደረጉ ኢትዮጵያዊነትን በመርገጥና በመጫን፤ ሀገሪቱንና ሕዝቧን ችግር ላይ ጥለዋል። በሀገር ክልል ውስጥ ያሉ ሁሉ፤ በኢትዮጵያዊነቱ አንድ ሕዝብ አንድ ዜጋ ነው። የተለያዩ ሀገር (ስቴት) በኢትዮጵያ ውስጥ የለም። ስቴቷ ኢትዮጵያ ናት። በአንድ ሕዝብነቱ ደግሞ መንግሥት አቋቁሞ ለሶስት ሺህ ዓመታት የኖረ፤ በታሪክ የታወቀና የተደነቀ ህዝብ ነው። ሀገር ያጠፋ አመለካከትና ቋንቋ ከእንግዲህ ቦታ ሠጥተን፤ በኢትዮጵያ ምድርና በሕዝባችን ላይ ሌላ ትርምስና ስህተት አይደገምም። ሕዝብ ወደፊት ይወስናል እያሉ የወያኔ/ሸዓቢያን ኢትዮጵያን የማፍረስና ሕልውና የማሳጣት ተልዕኮን ማሳካት ማንም አይችልም።

ለዚህ ኢትዮጵያን ለማፈራረስና ሕዝቧን ለማወክ ሀገራችንን ለድርድር ለቅርጫና ለሕልውና ማፍረስ ተግባር የኅብረት ሰነድ በጋሪዮሽ ፈርመው የሚንቀሳቀሱ ሁሉ፤ እንዲሁም እገዛና አመራር እየሠጡ ያሉት ወያኔና ሸዓቢያ፤ በአሀዳዊ እናት ሀገር ኢትዮጵያ፤ በማይገሠሠው ሉዓላዊ ሕልውና ላይ ክህደት እንደፈጸሙ ታውቆ፤ በትሪዝንና በጎጠኛ ጀኖሳይድ ወንጀሎች በብሔራዊ ደረጃ ለፍርድ የሚቀርቡበት ጊዜ ቁልጭ ብሎ ተቃርቧል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገው ደግሞ አሀዳዊ ሀገሩን ኢትዮጵያን፣ ኢትዮጵያዊነቱን፣ ሰንደቅ ዓላማውን ነው። ወያኔን መገርሰስ፣ ሥርዓቱን ማፍረስ፣ የቋንቋና የጎጥ ክልሎችን ማጥፋት፣ ሀገርን ማዳን፣ የሕዝብና የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ . . . ወ.ዘ.ተ. ነው።

ከዚህ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ለኢትዮጵያ ህዝብ ጩኸትና ለቅሶ ምላሽ ለመሥጠት ታግሎ ለማታገል፤ በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጪ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ መሰብሰብ ከጀመሩ ቆይቷል። ነገር ግን አብዛኛው የመረጡት የትግል ጎዳና በቂ ሆኖ ስላልተገኘ፤ የብዙዎቹ ድርጅቶች አባላት ለከፍተኛ ጥቃት ተጋልጠዋል።

የኢትዮጵያን ታሪክ ዛሬም ሆነ ለመጪው ትውልድ መብቱን አስከባሪ የሆነ ኢትዮጵያዊ አቋም በመመሥረት ትግሉን በፍጥነት በማካሄድ ወያኔ የሚፈጽመውን በደልና ሴራን ለማክሸፍና ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ለማዳን የሚያስፈልገውን የትግል አርምጃ ለመውሰድ ለመደራጀት መነሳት ዛሬ አሁን ነው።

ውርደትና ሽንገላን የመቀበል ፀባይና ልምድ የሌለን እኛ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆቿ እንደ ቀደምት ትውልዶች እምቢኝ ለሀገሬ፣ ለአንድነቴ፣ ለታሪካዊ ቅርስና ውርሴ፣ ለሰንደቅ ዓላማዬ፣ በማለት የማይታጠፍ ቃል ኪዳን ገብተን፤ በጎጥ እብሪት የተወጠረውን የወያኔን አገዛዝ ማንበርከክና ማስወገድ አሁኑ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብና የሀገር ወዳድ ኃይላት ቀዳሚና ያለመ ትኩረት ድርድር ሳይሆን ወያኔን፣ ርዕዩቱን፣ ሥርዓቱን፣ መዋቅሩንና ድርጊቱን ሁሉ ጠራርጎ ሕልውናውን ማሳጣትና ያገርን ትንሳዔና ኢትዮጵያዊነትን ማረጋገጥ ነው። ስለዚህ ለሀገር አንድነት የቆማችሁ ግለሰቦች፣ ስብስቦችና ኃይሎች ሁሉ፤ ከሕብረት መካን ፖለቲካ ከማድረግ ተጽዕኖዎች ራሳችሁን በአስቸኳይ አላቃችሁ፤ በድህረ-ወያኔ ለሚጠብቃችሁ ያገርና የወገን ግዳጅ ሀገር ምሥረታ ዝግጁ በመሆን ለትብብርና ለተግባራዊ እንቅስቃሴ በአንድነት እንዝመት።

ስለሆነም የእስከዛሬው የተቃዋሚ ጎራ የሃያ ሶስት ዓመት ጉዞ እንኳን ብሔራዊ ሥልጣን ሊይዝ ቀርቶ ሀገሪቱን፣ ሕዝቧን፣ አንጡራ ሀብቷንና ሌሎች ብሔራዊ ጥቅሞቿን ሊያስከብር ከቶ አልቻለም።

ለኢትዮጵያ፣ ለሕዝቧና ለብሔራዊ ጥቅሞቿ ቀዳሚ ትኩረት በመሥጠት ለሀገርና ለፖለቲካው ሊጠቅሙ የሚችሉትን ሁሉ ከእያቅጣጫው እያፈላለጉ አንድ ወጥ ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅት ተፈጥሮ በዓለም አቀፍ እውቅና አግኝቶ ሀገርና ሕዝብን በማዳን ኢትዮጵያዊ መንግሥት እንዲፈጠር መሆንና መቻል አለበት። ወያኔም የሚፈራው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የያዘ ድርጅት ስለሆነ፤ ወያኔን ለማጥፋት በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የተመሠረተ ድርጅት መፈጠር አለበት።

በሕዝብ ያመነ፣ ሕዝብን መሠረት ያደረገ፣ ሕዝብ ያቀፈ፣ የሕዝብን ቁጣ የሚያነድና አብሮ በግብታዊነት የሚያምጽ፤ ምንጊዜም ድልን ይቀዳጃል። ምክንያቱም ቁልጭ ያለ ሀቅ ነው። የማንኛውም ፀረ-መንግሥት ትግል መሠረቱ ወሳኝና ታሪክ ሠሪው ኃይል ምንጊዜም ሕዝብ ነው። ሕዝብ በግብታዊነት ከተነሳ፤ እንደ እባብ ይነድፋል፣ እንደ እፍኝትም መርዙን ነስንሶ ዒላማውን በመደምሰስ ሥር ነቀል ለውጥ ያመጣል።ዴሞክራሲያዊ-ሰብዓዊ መብትን ለማስከበር፤ ለአንድ ሀገር የአንድነት ብልጽግናና ኃይልን ማስተባበር እንጂ፤ መገነጣጠልና ትንሽ አድርጎ መሸራረፍና ማዳከም፤ የኅብረተሰብ ትግል ሳይሆን፤ የከፋፍለህ ግዛው ፋሽስት ሥርዓት ነው። ወያኔ ማለት ይህ ነው። ዴሞክራሲ ደግሞ ከመንግሥት የሚሠጥ፣ መንግሥት ነኝ ያለ የሚሠራው ወይንም የሚያደርገው አይደለም። ዴሞክራሲ ሕዝብ የሚሠራው ለተግባራዊነቱ የሚያረጋግጠውና የሚፈፅመው ነው። ዴሞክራሲ የሚሠራው በሕዝብ ነው። ለዚህም ነው ሕዝብ በፅናትና በቆራጥነት የሚታገለው። ለዚህ ክቡርና ወቅታዊ ዓላማ ዕውን መሆን በቆራጥነትና በፅናት የሀገራዊ እምነትና ታሪክ ላይ ብርቱ ኢትዮጵያዊነት ለአላችሁ ሁሉ ታግሎ ለማታገልና ኢትዮጵያና ሕዝቧን ከወያኔ ነፃ ለማውጣት የትግሉ አጋርና ተካፋ እንትሆኑ ጥሪ አቀርባለሁ።

ዓላማው፤

፩. በኢትዮጵያ ሕዝብ ሙሉ ድጋፍና ተሳትፎ በማድረግ ቁርጠኛ ትግል ሀገሪቱንና ሕዝቡን አደጋ ላይ የጣለውን የወያኔን የጭቆና ቀንበር አገዛዝ በአፋጣኝ ከሥልጣን ማስወገድ፤

፪. የኢትዮጵያ የየብስ፣ የባህርና የአየር ብሔራዊ ክልልና ሉዓላዊነት መጠበቅ፤

፫. ሀገሪቱን በጎሳ ቋንቋ ልዩነት ተፅዕኖና ሃይማኖት ነፃ ማድረግና ክልሎችን (በቋንቋ) በማጥፋት አንድነቱን በእኩልነትና በመከባበር ላይ መመሥረት፤

፬. በኢትዮጵያ የሰላም ዴሞክራሲ በመፈቃቀድና በመከባበር ላይ የተመሠረተ የሕዝብ እኩልነትና አንድነት ለሀገር ሉዓላዊነት ማረጋገጥ ነው።

ተቀዳሚውና ወሳኝ አጀንዳችን ኢትዮጵያና ሕዝቧን ማዳንና ነፃነትና የዜግነት መብትን ማስበር ነው። ለዚህ ትግሉን በተደራጀ ኃይል ለፋፋም የወቅቱ አጣዳፊ ጉዳይ ነው ።ይህን መልዕክት የተቀበለ ኢትዮጵያዊ ተግባርነቱ አስተያየትና ለመወያየት የፈለግ በዚህ ኢሜል ይላኩ

belay211@gmail.com

*ምንጊዜም አገርና ሕዝብ ያሸንፋል !*